# <u>በዋሽንግተን ዲሲ ለአርቲስት ታማኝ በየነ ታላቅ የክብር ምሽት ተደረገ</u>

እሁድ ጁን 27 ቀን 2010 አንድ ታላቅ ታሪካዊ ምሽት ቨርጂኒያ በሚገኘው የሂልተን ሆቴል አዳራሽ ውስጥ እጅግ ደማቅ በሆነ ሁኔታ ተከናውኖአል። ክፍተኛ ቁጥር ህዝብ የተገኘበት የዚህ ዝግጅት ዓላማ የሀገር አንድነትና የህዝብ ነጻነት ጠበቃና ኮከብ አርቲስት ታማኝ በየነን ለማክበር ነበር።



ከአውሮፓ ድረስ ለዝግጅቱ በመጡና በዋሽንግተን ዲሲ አካባቢ የሚኖሩ ታዋቂ ግለሰቦች ምሁራን የጥበብ ባለሙያዎች ወዳጆቹ ወጣቶች

አዛውንት ሴት ወንዱ በተሰበሰበበት ተወዳጁ ባለሙያና የሰበዓዊ መብቶች ጠበቃ ታማኝ በየነ በስፍራው ሲደርስ ድምጻዊው ደረጀ ደገፋው በሙዚቃ ባለሙያዎች በመታጀብ ለምሽቱ አዲስ ባዘጋጀው ልዩ በእጅጉ በሚቀሰቅስ ዜማ

*ታማኝ በየነ ይሄው አለ፤*

*ህገሬን ወገኔን ስንደቄን እንዳለ፡*

*ነጻነት እኩልነት አንድነት እያለ፡*

*ኢትዮጵያ ህገሬን አትንኩ እንዳለ፤*

ሲቀበለው በአዳራሹ ውስጥ የተገኘው ህዝብም ከመቀመጫው በመነሳት በጭብጨባና በሆታ አጅቦታል። ታማኝም ይህን የህዝብ ፍቅርና አቀባበል በማየት በደስታ እምባው በዓይኑ ሞላ። ከባለቤቱ በፋንትሽ በቀለና በሶስት ልጆቹ ታጅቦ ቦታውን እንደያዘ እራት እንዲመገቡ ተደርጎ ዋናውና መደበኛው ፕሮግራም ተጀመረ።

የተለያዩ ድምጻውያን መድረኩን ተረክበው በሀገረሰብና ጨዋታና በዘመናዊ ዜማዎች ታዳሚውን ሲያዝናኑ ከቆዩ በኋላ የእለቱ የክብር ምሽት የመድረክ መሪና የታማኝ በየነ የረጅም ዘመን የሙያ ጉደኛ ዓለም ፅሀይ ወዳጆ ከውልደት እስከ እድገት የታማኝን ሙያዊ ታሪክ፤ ለህገር አንድነትና ለህዝብ ነጻነት ያደረገውን ከፍተኛ አስተዋጻኦ የሚዘክር ንግግር አደረገች።



በመቀጠልም የብሄራዊ ትያትር ዋና ስራ አስኪጅ አዘጋጅና ከያኒ አቶ ጌታቸው አብዲ ታማኝና የኪነ ጥበበ መድረክ በሚል ርእስ ስለ አርቲስት ታማኝ በየነ ያላቸውን ትዝታና በሙያው ያለውን ልዩ ተሰጦ እንዲሁም ለህዝብና ለህገር ደከምኝ ስለቸኝ ሳይል እንደሌሎች በሃገርና በህዝብ ጠላቶች ጉያ ሳይግባ በጽናት የቀጠለ ታላቅ ኢትዮጵያዊ መሆኑን ገልጸው ምሳሌዎችንና ትዝታዎችን በማንሳትም ታዳሚውን ያሳቀና ያዝናና ግሩም ንግግር አደረጉ። የአሜሪካ ድምጽ (VOA) የአፍሪካ ፕሮግራም ሥራ አስኪያጅ የሆኑት አቶ ንጉሴ መንገሻም በበኩላቸው ታማኝን ካወቁት ጀምሮ ለአርቲስት ታማኝ ያላቸውን ክፍተኛ አክብሮትና አድናቆት ገልጸው የኢትዮጵውያን ከተባበሩ ምንም ነገር ለማድርግ እንደማያዳግታቸው የምሽቱ ደማቅና ልዩ ዝግጅት ራሱ አንድ ምስክር መሆኑን በማስመር አጭር ንግግር

አደረጉ። እውቁ የስነ ጽሁፍ ሰው ሻለቃ ክፍሌ አቦቸርም በበኩላቸው ታማኝ በየነና የሀገር ፍቅር ስሜቱ በሚል ርእስ ዙሪያ ያዘጋጁትን አስደመጡ።



በእለቱ ከተለያዩ አህጉራት የተላኩ የምስጋናና የደስታ መግለጫዎች በየፕሮግራሙ ጣልቃ ይነበቡና ይቀርቡ ነበር። ኖርዌ ከሚገኙ ኢትዮጵያውያን የተላከ አበባ ፤ ከኖርዌ እንዲሁ ከታወቁት የስነ-ጽሁፍ ሰው ከአቶ አበራ ለማ የደስታ መግለጫ፡ ከለንደን "የአቢስኒያ ኮከብ" ሜዳሊያ አቶ አለባቸው የላኩ ሲሆን ለንደን ከሚገኙ ኢትዮጵያውያንና ከሊቀ መምህራን አበባው ይግዛው የታላኩ የደስታ መግለጫ መልክቶች፡ ገጣሚ ኀናቻው *"ታማኝ ሰው"* ሚል ርእስ ያጻፉት ስንኝ ተነቦአል። በአውሮጳ የሚገኙ ኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያውያን ማህብራትም የላኩት መልክት እጅግ በሚጥም መልክ የተላለፈ ሲሆን፤ ከኮሎምቦስ - ኦሃዮ ደግሞ ከልሳነ ግፉአን ማህብር (*VOICE OF THE VICTIMS*

*ORGANIZATION*) የተላከ የደስታ መግልጫ ደብዳቤና ስጦታ በማህበሩ ተወካይ አማካኝነት ለታማኝ ተበርክቶአል። ክሰቶኮልም ስዊድን ነዋሪ ኢትዮጵያውያንና ከሬድዮ ኢትዮጵያ አዘጋጆች መልክቶች እንዲሁ ግጥም የቀረበ ሲሆን በሰሜን አሜሪካ ላለፉት 17 ዓመታት የማህበረሰቡን አገልጋዮች በማድነቅና በማክብር የሚታውቀው የሲድ (*SEED*) ሊቀመንበር የሆኑት ፕሮፌሰር መላኩ ላቀው የተላከ ደብዳቤም ተነቦአል። በፕሮግራም ጥበት ምክነያት ሙሉ በሙሉ መቅረብ ባይችሉም የደስታ መግለጫ መልክቶች ከካናዳ ፡ አንጋፋው የስፖርት ባለሙያ አቶ ግርማ ቸሩ እንዲሁም ልጅ ተክሌ፡ ከካሊፎርንያ ፕሮፌሰር አዱኛው ወርቁ፣ ከዋሽንግተን ዲሲ አቶ መኮንን ዘለለው በትግርኛና በአማርኛ መልክት ከሚኒሶታ ፈቃደና የኢትዮጵያውያን ተማሪዎች ከሲያትል አቶ አብረሃ በላይና አቶ ሼክስፒር ፈይሳ ፡ እንዲሁም ከሌሎች ቦታዎች ተልከዋል።



የሀገር ፍቅር በውስጡ የሚንቦገቦግውና የኢትዮጵያን ሰንደቅ በከፍታ መውለብለብን ዘወትር የሚመኘው ታማኝ ለቀድሞ የኢትዮጵያ ሠራዊት መከበርና ሞገስ ላደረጋቸው ክፍተኛ አስተዋጻኦም የቀድሞ አየር ሀይል መረዳጃ ማህበር ሊቀመንበርና  በሰሜን አሜሪካ የጀግኖች ክብረ በዓል አዘጋጅ ኮሚቴን በመወከል የሁለቱም ማህበራት ሊቀመንበር  አቶ ብርሃኑ ሞላና የቀድሞ ሥራዊት ማህበር ተወካዮች ለታማኝ የተዘጋጀለትን ስጦታ በልዩ ሥርዓት በማቅረብ ለበዓሉ ክፍተኛ ደምቀት ሰጥተውታል።

በቅርቡ ከኢትዮጵያ የኪነ ጥበብ መድረክ የተለየው የታላቁ ንጉስ የጥላሁን ገሠሠ ልጅ ንጹህ ብር ጥላሁን በሥፍራው በመገኘት “አባታችን ጥላሁን ከአሉት ልጆቹ የማይነጥለው ልጁ የኛም ወንድማችን ነው” በማለት ውድ አባት ከሀገር ሲወጣ የሰጣትን የወርቅ ቀለበት ከጣት አውልቃ ለታማኝ አበረከተችለት። ንጹህ ብር ጥላሁን የተገኘውን ህዝብ ስሜት የጫረ ንግግር አድርጋለች።



የታማኝን ፈለግ በመከተል ከወጡት ወጣት ኮሜዲያን መካከል መስከረም በቀለ ከሌላዋ ታዋቂ የመድረክ ባለሙያ ከአልማዝ ጥላሁን ጋር በመሆን ህዝቡን በሳቅ ያስደስቱት ሲሆን የተወዳጁ ባለሙያና የህዝብ መብት ጠበቃ የታማኝ በየነ  የህይወት ጎዞን በሚመልከት የተቀናበረ ፊልም ታይቶአል።

ከኢትዮጵያ ከቤተሰቡና ከባለሙያ ወዳጆቹ የተላኩንትም መልእክቶች በፊልም ተቀናብረው ሲታይ እጅግ አስገራሚና ውብ ነበሩ ። በምሽቱ መድረኩን ለመካፈል የተገኙት ድምጻውያን ብዙ ሲሆኑ በጊዜ እጥረት ሳቢያና በፕሮግራም ብዛት መጨናነቅ ሁሉንም ለማሳተፍ አልተቻለም ነበር።

በመጨረሻም የቀድሞው የባህልና የስፖርት ጉዳይ ሚኒስቴር ሚኒስትር ሻለቃ ግርማ ይልማ ከሲያትል ዋሽንግተን በመምጣት በስፍራው በመገኘት የታማኝ በየነን የአክብሮት ቀን አስፈላጊነት አስመልክተው ንግግር አድርገዋል፡ ሽልማትም አበርክተዋል። በዝግጅት ኮሚቴው የተዘጋጀውን ክፍተኛ ግምት የሚሰጠው ሽልማትም በመቀበል ባለሙያው ታማኝ በየነም የተሰማውን ደስታና ለተድረገለትም ክፍተኛ ግምት ለሚሰጠው ምሽት ጥልቅ ምስጋናውን በማቅረብ የእለቱ ፕሮግራም ተጠናቆአል።

*ታማኝ በየነ ይሄው አለ፤*

*ህገሬን ወገኔን ስንደቄን እንዳለ፡*

*ነጻነት እኩልነት አንድነት እያለ፡*

*ኢትዮጵያ ህገሬን አትንኩ እንዳለ፤*





